የሥራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ I አጠቃላይ መግለጫ		
የመስሪያ ቤቱ ስም	የሥራ መደቡ መጠሪያ	የሥራ ዘርፍ/የሥራ ሂደት
ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	ቤተሰብ ጤና ፕሮፌሽናል II	ህብረተሰብ ጤና
	በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር.ቢሮ ብቻ የሚሞላ	
የቅርብ ኃላፊ የሥራ መደብ/ተጠሪነት	የሥራው ደረጃ	የሥራው ኮድ
	XII	
መስሪያ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ		
በየደረጃው ባሉ ጤና ተቋማት		

II. የሥራ መደቡ ዋና ዓላማ፣ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት

2.1. የሥራ መደቡ ዓላማ፡-

- በፈውስ ሕክምና አገልግሎት ለሕሙማን በምርመራና ሕክምና በማድረግ፣ በተሀድሶ ሕክምና ለአካላዊ ጉዳተኞችና ህሙማን ድጋፍና ክብካቤ በማድረግ፣ በመከላከል ሕክምና ጤናን በማጎልበት እና በሽታን በመከላከል በበሽታ የተጠቁ ህሙማንን እና የድንገተኛ አደጋ ጉዳተኞች ስቅይ መቀነስ፣ ወደ ጤናማ ኑሮአቸው መመለስ፣ ሞትና አካል ጉዳትን በመቀነስ፣ ንቃተ ጤና በማበልፀግ፣ የበሽታን ስርጭት በመከላከል የሕብረተሰቡን ጤና ማሻሻል ነው።

2.2. ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት

ውጤት **1**፡ የመረጃ ጥራት ማረጋገጥ፣ የቤተሰብ ጤና ገፅታን መተንተን፣ ዕቅድ ማዘጋጀትና አፈፃፀምን መገምገም

- በየወቅቱ የሚሰበሰቡ፣ የሚጠናቀሩና ሪፖርቶች የሚደረጉ መረጃዎችን የተመሰከረ የጥራት ደረጃና መስፈርት በመጠቀም የመረጃዎችን ጥራት ይመረምራል፣ በተገኙ የጥራት ችግሮችና ውስንነቶች ላይ ግብረ መልስ ይሰጣል፣
- በበቤተሰብ፣ ማህበረሰብና አካባቢ መረጃ ላይ ተመስርተው በተለያዩ አመታት የተዘጋጁ የጤናና ጤና ተዛማጅ ገፅታን ታደራጃለች፣ የትንተና ጉዳዮችን ትለያለች፣
- የትንተና ጉዳዮችን መሰረት በማድረግ በቤተሰብ፣ በማህበረሰብና በአካባቢ ደረጃ ያሉ በጤናና ጤና ነክ መልካም አጋጣሚዎና ውስንነት ያለባቸውን ጉዳዮች በመተንተን ዋና ዋና ችግሮችን ይዘረዝራል፣
- ማህበረሰብ አቀፍ የጤናና ጤና ተዛማጅ ስትራተጂክ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ከማህበረሰቡ ጠቃሚ የሆኑ ድርጊቶችን በመለየት የማስፈፀሚያ ስልት ይቀይሳል፣ አስፈላጊ ግብአት ፍላጎትን ያመላክታል፣
- ከስትራተጂክ ዕቅድ የተቀዳ አመታዊ የድርጊት መርሀ ግብር ያዘጋጃል፣ ተፈላጊ ግብአትም እንዲሟላ ያደርጋል፣ የክንውን መከታተያ ቅፅ ያዘጋጃል፣ በዕቅድ የተያዙትን ተግባራት ያከናውናል፣
- ወርሃዊ፣ የሩብ አመት፣ የግማሽ አመትና አመታዊ የዕቅድ አፈፃፀምንን ይገመግማል፣ ያሉትን ጥንካሬ፣ ድክምት፣ መልክም አጋጣሚና ስጋት ይለያል፣ ይህንን መሰረት በማድረግ እንደአስፈላጊው የዕቅድ ክለሳ ያደርጋል፣

ውጤት **2**፡ በፈውስ ሕክምና አገልግሎት ለሕሙማን ምርመራና ሕክምና ማድረግ

- በአጣዳፊና አዝጋሚ በሽታ የተያዙ ህሙማን ይጎበኛል፣ የተለያዩ የምርመራ ስልቶችን በመጠቀም ስለሕመሙ ሁኔታ ሙሉ ቃል ይቀበላል (history taking)፣ የሰውነት አሰራር መሰኝ ምልክቶች ይለካል (measure vital sign)፣ ሙሉ የሰውነት